በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት አፈፃፀም እና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሣሥ/2003
አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የአሠራር ሂደት (PROCESS DISCRIPTION) 3

ክፍል ሁለት 7

የኦዲት ግኝቶች 7

ሀ.የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን ተፈፃሚ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት አደረጃጀት መፍጠራቸውን እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋታቸውን በተመለከተ፤ 7

ባለድርሻ አካላት የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን ለማስፈፀም ያላቸው አደረጃጀትን በተመለከተ፤ 7

የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በረጅም እና በአጭር ጊዜ ዕቅዱ ውስጥ ማካተቱን በተመለከተ፤ 8

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ሲያስተናግዱ የወጪ መጋራት ክፍያን ማጠናቀቃቸውን የሚያረጋግጡ መሆኑን በተመለከተ፤ 9

የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ሂሣብን ለመሰብሰብ የዘረጋውን የአሠራር ሥርዓት በተመለከተ፤ 10

የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተሰብሳቢ ሂሣብ ስሌት፣ አሰባሰብ እና ፈሠስ አደራረግን በተመለከተ፤ 11

የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን የሚመለከቱ መረጃዎች በዳታ ቤዝ የሚይዝ መሆኑን በተመለከተ፣ 13

ከወጪ መጋራት ተጠቃሚ የወር ደመወዝ አሠሪ ድርጅቶች 10% (1/3ኛ) ተቀናሽ ማድረጋቸውን እና በወቅቱ ፈሠስ ማድረጋቸውን በተመለከተ፤ 13

ለ. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን ተፈፃሚ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት እና ወጥ በሆነ መልኩ የሚሰሩ መሆኑ እንዲሁም ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋታቸውን በተመለከተ፤ 15

የትምህርት ሚኒስቴር ደንብ ቁጥር 154/2000 ለማስፈጸም ያወጣውን መመሪያ ለባለድርሻ አካላት የሚያሰራጭበትን መንገድ በተመለከተ፤ 15

የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተመረቁ እና ያቋረጡ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን እንዲያሳውቁት ስለማድረጉ፤ 15

የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን ተፈፃሚነትን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጣቸው ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ መፍጠራቸውን በተመለከተ፤ 16
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚያስተላልፉትን ሪፖርትን በተመለከተ፤ 17
የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሰጠው ውክልና እና በውክልናው መሠረት መሰራቱን በተመለከተ፤ 17
የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መስጠቱን በተመለከተ፤ 18
የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በተመለከተ ለባለድርሻ አካላት ስለሚያስተላልፈው መረጃ፤ 19
የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚን የሚቀጥሩ አሰሪ ድርጅቶች ተጠቃሚዎች ከተቋማት ጋር የገቡትን ውል የሚያሳይ ማስረጃ መጠየቃቸውን እና በየ3 ወሩ ዝርዝራቸውን ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሪፖርት ማድረጋቸውን በተመለከተ፤ 20

ክፍል ሦስት 22

የመደምደሚያ ሀሣቦች 22

ክፍል አራት 24

የማሻሻያ ሀሣቦች 24

አባሪ 1 I

አባሪ 2 IV

ክፍል አንድ
መግቢያ

1. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ሥራ የሚከታተለው የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ነው፡፡ የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ማለት ተጠቃሚው መንግስት ከሚያወጣው መጠነ ሰፊ የትምህርት ወጪ ውስጥ የተወሰነውን ወጪ እንዲሸፍን ለማድረግ የሚያስችል ስልት ነው::

2. በሀገራችን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እና የአለማያ እርሻ ኮሌጅ ተቋቁመው ትምህርት መስጠት ሲጀምሩ የተማሪዎችን የትምህርት፣ የምግብ፣ የመኝታ እና የህክምና ወጪዎችን ሙሉ በሙሉ መንግስት በመሸፈንና የኪስ ገንዘብ በመስጠት ተማሪዎች እንዲማሩ ይደረግ ነበር:: ይሁን እንጂ የከፍተኛ ትምህርት ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ በመሆኑ እና በየትምህርት ደረጃው ፍትሐዊ የሆነ የትምህርት በጀት ክፍፍል በማስፈለጉ የከፍተኛ ትምህርት ወጪን ተጠቃሚዎች እንዲጋሩ በማድረግ መንግሥት የሚመድበውን የፋይናንስ አቅም በመገንባት ትምህርት ለህብረተሰቡ እንደሚሰጠው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አመዛዝኖ በመመደብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን፣ የቴክኒክ እና ሙያ እንዲሁም የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲስፋፉ በማስፈለጉ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 351/95 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 650/2001 እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 91/95 መሠረት ማንኛውም በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ እና ከ1996 የትምህርት ዘመን ጀምሮ በከፍተኛ የትምህርት ተቋም ውስጥ ትምህርቱን በመከታተል ላይ የሚገኝ ተማሪ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ደንብ እንደሚመለከተው ተደንግጓል::

3. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ደንብ ቁጥር 91/95 በወጣበት ወቅት 9 /ዘጠኝ/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 22 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይገኛሉ፡፡

4. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ደንብ ቁጥር 91/95 የህግ ክፍተት እና የአፈፃፀም ችግሮች እንዳለበት በባለድርሻ አካላት አስተያየት በመሠጠቱ የነበሩትን ችግሮች እና ክፍተቶች በማስተካከል የቀድሞው ደንብ ተሻሽሎ በደንብ ቁጥር 154/2000 ተተክቶ ተግባራዊ እንዲደረግ ተደንግጓል::

የፋይናንስ ምንጭ

5. በሀገሪቷ ለሚገኙ 22 ዩኒቨርስቲዎች በ2000፣ በ2001 እና በ2002 ዓ.ም እንደቅደም ተከተላቸው ብር 1,195,187,800፣ ብር 1,645,375,300 እና ብር 2,411,059,800 በድምሩ ብር 5,251,622,900 ከመንግስት ተመድቦላቸዋል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ዓላማ

6. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ዋና ዓላማ የከፍተኛ ትምህርት ወጪን ተጠቃሚዎች እንዲጋሩ በማድረግ መንግስት የሚመድበውን የፋይናንስ አቅም በመገንባት ትምህርት ለህብረተሰቡ እንደሚሰጠው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አመዛዝኖ በመመደብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመላው አገሪቱ ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲስፋፉ በማድረግ የትምህርት ስርጭቱን ፍትሐዊ እንዲሆን ማድረግ ነው።

የአሠራር ሂደት (PROCESS DISCRIPTION)

የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት የሥራ ሂደት መግለጫ

በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ደንብ ቁጥር 154/2000 መሰረት፡-

የትምህርት ሚኒስቴር

7. የትምህርት ሚኒስቴር ደንቡ ስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከተጠቃሚዎች የሚጠየቁትን የክፍያ ተመን ያፀድቃል፤ ለዚህ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፣ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

8. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ስራ የሚከታተል የስራ ክፍል በማደራጀት በተጠቃሚዎች የሚፈፀሙትን የቅደሚያ ክፍያ በመሰብሰብ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም በየትምህርት ዘመኑ ተመራቂዎችን እና ያቋረጡ ተማሪዎች ዝርዝርን በተጨማሪም ከእያንዳንዱ ተጠቃሚ የሚፈለገውን የወጪ መጋራት የገንዘብ ዕዳ ወይም የአገልግሎት ግዴታ የሚያሳይ ሰነድ አዘጋጅተው ለትምህርት ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ለወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ይሰጣሉ።

አሰሪ ድርጅቶች

9. ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚን የሚቀጥር አሰሪ ድርጅት ተቀጣሪው ከተማረበት ተቋም የተሰጠውን የሚፈለግበትን የክፍያ መጠን የሚገልፅ ማስረጃ በመቀበል ተጠቃሚው ስራ ከያዘ ከ6 ወር በኋላ በየወሩ ከደመወዙ አስር በመቶ /10%/ ወይም ከ1/3 የማይበልጥ በመቀነስ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያስተላልፋል እንዲሁም የተቀጣሪዎችን ዝርዝር በየ3 ወሩ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ያሳውቃል።

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

10. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አጠቃላይ ክፍያን ይሰበስባል፣ የአፈፃፀም ስርአት በመዘርጋት አፈፃሙን ይከታተላል እንዲሁም ከክፍያ አሰባሰብና አፈፃፀም ጋር

በተያያዘ መመሪያዎችን ያወጣል፤ ለዚሁም ተፈፃሚነት አስፈላጊውን ስርአት እና አደረጃጀት በመፍጠር ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

የኦዲቱ አላማ

11. የኦዲቱ አላማ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ክፍያን እንዲሰበስቡ እና አፈፃፀሙን እንዲከታተሉ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን እና በቅንጅት መስራታቸውን፣ በባለድርሻ አካላቶች መካከል ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርአት መኖሩን እና የወጪ መጋራት ክፍያ ደንቡ በሚያዘው የጊዜ ገደብና ስርዓት መሠረት መሰብሰቡን እና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፤ ይህንን በተመለከተ ያሉትን የአሰራር ችግሮች በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

12. ኦዲቱ የሸፈነው በሦስት በጀት ዓመታት ማለትም ከ2000 እስከ የ2002 በጀት ዓመታት ባለው ጊዜ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በተመለከተ የተሠሩትን ሥራዎች ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በዋናነት በትምህርት ሚኒስቴር ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን፣ የክልል የፋይናንስ ቢሮዎችን፣ አሠሪ ድርጅቶችን እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በናሙና መርጦ በማየት የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት የሥራ ሀላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ መጠይቆችን በመላክ እና አሠራሩን በአካል ተገኝቶ በማየት ነው፡፡

13. በዚህም መሠረት የወጪ መጋራት ክፍያ ከሚመለከታቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ በአማራ ክልል የሚገኙ ሁለት ዩኒቨርስቲዎች /ጎንደር እና ባህርዳር/፣ በኦሮሚያ ክልል ከሚገኝ 1 ዩኒቨርሲቲ /አዳማ/፣ በደቡብ ክልል ከሚገኙ 2 ዩኒቨርሲቲዎች /ሐዋሣ እና ዲላ/ እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ጨምሮ በድምሩ በስድስት ዩኒቨርስቲዎች በመገኘት መረጃዎች ተከልሰዋል፡፡ ለኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ ቀርቧል፡፡ እንዲሁም በናሙና ለተመረጡ 15 የመንግስት መ/ቤቶች፣ 14 የግል ድርጅቶች፣ 9 የልማት ድርጅቶች እና 15 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGOs) በድምሩ ለ60 አሰሪ ድርጅቶች መጠይቅ የተላከ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 22 አሠሪ

ድርጅቶች ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ሲቪል ሠርቪስ ኤጀንሲ፣ አዋሽ ባንክ፣ ወርልድ ቪዥን እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአካል በመገኘት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ለኃላፊዎችም ቃለ-መጠይቅ ቀርቧል፡፡ የኦዲት ቡድኑ በኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን አዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ ሀዋሣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ ባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በኦሮሚያ ክልል ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ በአማራ ክልል ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በአካል በመገኘት መረጃዎች ከልሷል፡፡ ለኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ አቅርቧል፡፡ አሠራሩን በአካል ተገኝቶ ተመልክቷል፡፡

የኦዲቱ አካባቢ

14. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት በደንቡ መሠረት በአግባቡ መፈፀሙንና እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫ /Main audit issue/

15. ከላይ በተገለፀው ኦዲት አካባቢ ሥር ሁለት ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን በመጀመሪያው የትኩረት አቅጣጫ ሥር አራት ንዑስ የኦዲት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም:-

1. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በተመለከተ የወጡ አዋጆች እና ደንቦችን ተፈጻሚ እንዲያደርጉ ስልጣንና ኋላፊነት የተሰጣቸው ባለድርሻ አካላት የደንቡን ተግባራዊነት እና ውጤታማነት ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርአት የዘረጉ መሆኑን ማረጋገጥ፤

   1.1. የትምህርት ሚኒስቴር በደንቡ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ለመወጣት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን እና በዚሁ መሠረት ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን ማረጋገጥ፣

   1.2. በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የሚፈለግባቸውን የክፍያ ዕዳ ግዴታ አሰባሰብ

ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር እና ለማስፈፀም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን እና ተግባራዊ ማድረጉን ማረጋገጥ፤

1.3. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በደንቡ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ለመወጣት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጉ እና በዚሁ መሠረት ሥራውን እየተወጡ መሆኑን ማረጋገጥ፤

1.4. ከመንግስት ተቋማት ተመርቀው የሚወጡ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ቀጥረው የሚያሰሩ አሰሪ ድርጅቶች በደንቡ መሰረት የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት እየተወጡ መሆኑን ማረጋገጥ፤

2. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወጪ መጋራት አዋጆችን እና ደንቦችን ተፈፃሚ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የሚሰሩ መሆኑን እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርአት የዘረጉና ተግባራዊ ያደረጉ መሆኑን ማረጋገጥ፤

የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት

16. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሁለት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች እና አራት የኦዲት ንዑስ ትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 34 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) የተዘጋጁ ሲሆን የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት ለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት የወጡ አዋጅ እና ደንቦች በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ የአፈፃፀም መመሪያዎች እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት የተገኙ መመሪያዎች፣ መፃፃፎች እና ቃለ-መጠይቆች ናቸው:: በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የትምህርት ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸው አስተያየታቸውን አልሰጡም:: መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል::

ክፍል ሁለት
የኦዲት ግኝቶች

ሀ.የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን ተፈፃሚ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት አደረጃጀት መፍጠራቸውን እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋታቸውን በተመለከተ፤

ባለድርሻ አካላት የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን ለማስፈፀም ያላቸው አደረጃጀትን በተመለከተ፤

17. የወጪ መጋራትን ለማስፈፀም ስልጣን የተሰጣቸው ባለድርሻ አካላት የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን ተፈፃሚነት ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል አደረጃጀት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

18. የትምህርት ሚኒስቴር በአዋጁ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስፈፀም፣ ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር እና ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል አደረጃጀት ፈጥሮ አልተገኘም፡፡ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ዙሪያ የሚመጡ ጉዳዮችን በሕግ ክፍል በኩል ጊዜያዊ ምላሽ እንዲሰጥ የሚያደረግ ቢሆንም ይህንን ሥራ በአግባቡ ለመከታተል የሚያስችል ራሱን የቻለ አደረጃጀት እንደሌለው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

19. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለወጪ መጋራት ሥራ በባለሙያ ደረጃ ባስቀመጠው ሦስት መደብ ላይ የሠው ኃይል ያልመደበ በመሆኑ፣ የወጪ መጋራትን የተመለከቱ ሥራዎችን በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በተደራቢነት ክፍያ ሊፈጽሙ የሚመጡ ተጠቃሚዎችን ብቻ በማስተናገድ ይሠራ እንደነበር ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

20. ስለሁኔታው የባለሥልጣን መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠየቀው በሰጡት ምላሽ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምርክ ባለሥልጣን በአዲሱ አደረጃጀት መሠረት የሰው ኃይል ቅጥር የሚያካሂድ መሆኑን እና በባለቤትነት እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባለፉት ሁለት ዓመታት ሲካሄድ

በነበረው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ምክንያት ቀደም ሲል ለወጪ መጋራት የነበረው አደረጃጀት በመታጠፉ የክትትል ክፍተት ተፈጥሮ የነበረ እንደነበር፣ ሆኖም ግን የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ፈልገው ሲመጡ በሕግ ክፍል በኩል ምላሽ ይሰጥ እንደነበር ገልፀዋል፡፡

21. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ስድስት ተቋማት ውስጥ ሦስቱ (50%) ሀዋሣ ዩኒቨርስቲ፣ ዲላ ዩኒቨርስቲ እና ጎንደር ዩኒቨርስቲ ለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ራሱን የቻለ የሥራ ክፍል አቋቁመው አልተገኙም፡፡

22. በኦዲቱ ወቅት እንደተገነዘብነው ባለድርሻ አካላት ለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ትኩረት ባለመስጠታቸው እና የወጪ መጋራትን ሥራ ለማካሄድ ራሳቸውን ችለው የሚንቀሳቀሱበት አደረጃጀት ባለመፍጠራቸው ሥራው በአግባቡ እንደማይከናወን ነው፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በረጅም እና በአጭር ጊዜ ዕቅዱ ውስጥ ማካተቱን በተመለከተ፤

23. ትምህርት ሚኒስቴር በየጊዜው በሚያዘጋጀው ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ እና የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ዙሪያ የሚሠሩ ሥራዎችን ሊያካትት እና በሪፖርቶቹ መሠረት ለሚታዩ ክፍተቶች እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

24. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ ከከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት የሚሰበሰበውን ገንዘብ እንደገቢ ምንጭ ቢያሳይም የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ደንብን ውጤታማ ለማድረግ እንዲያስችል በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ዙሪያ ሊሠሩ የሚገባቸውን ተግባራት ከስትራቴጂክ ዕቅድ በመመንዘር በዓመታዊ ዕቅዱ እና የዕቅድ ክንውን ሪፖርቱ ውስጥ አካቶ አልተገኘም፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጁ የ1999 ዓ.ም. እና የ2001 ዓ.ም. የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች ውስጥ በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ዙሪያ የተሠሩ ሥራዎችን፣ ያጋጠሙ ችግሮችን እና የተወሰዱ እርምጃዎችን ያላካተቱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም የ2000 በጀት ዓመት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

25. ስለሁኔታው ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቆ በሰጠው መልስ ስለወጪ መጋራት በየመምሪያው በሚዘጋጅ ሪፖርት ውስጥ እንደሚካተት ገልፀው፣ በዓመታዊ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተው ሪፖርቱ የሚያተኩረው በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በመሆኑ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ለማረጋገጥ የየመምሪያው ዝርዝር ሪፖርት ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

26. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ1998-2002 ዓ.ም ባወጣው የትምህርት ሴክተር ልማት ፕሮግራም ስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ የወጪ መጋራትን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ ከ1999-2002 ዓ.ም. ከወጪ መጋራት በሚገኝ ብር 273,130,000. /ሁለት መቶ ሠባ ሦስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሠላሣ ሺህ/ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል አቅዶ የነበረ ቢሆንም የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከ1998-2002 ዓ.ም ከወጪ መጋራት የሰበሰበው ገንዘብ ብር 23,180,384. /ሃያ ሦስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሠማንያ ሺህ ሦስት መቶ ሠማንያ አራት ብር/ ብቻ መሆኑ ከመረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የትምህርት ሚኒስቴር ከያዘው ዕቅድ 8% ብቻ የተሰበሰበ መሆኑን ያሳያል፡፡ በባለሥልጣኑ የተሰበሰበው ብር 23,180,304. ለብቻው በተለየ የባንክ ሂሣብ ቁጥር ሣይለይ እንደማንኛውም ገቢ ወደ ትሬዠሪ ፈሠስ ተደርጓል፡፡

27. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ ወጪ መጋራትን በተመለከተ ያስቀመጠው ዕቅድ ተግባራዊ መሆኑን አለመከታተሉ እና በዓመታዊ ዕቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ የወጪ መጋራት በተመለከተ የሚሰሩ ሥራዎችን አለማካተቱ የወጪ መጋራትን ተፈፃሚነት ለመከታተል፣ ለማስፈፀም እና ለመቆጣጠር እንቅፋት ከመሆኑም ባሻገር ያጋጠሙ ችግሮችን ለይቶ ችግሮቹን ለማሻሻል እና የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ሲያስተናግዱ የወጪ መጋራት ክፍያን ማጠናቀቃቸውን የሚያረጋግጡ መሆኑን በተመለከተ፤

28. ተቋማት በደንቡ በተሰጣቸው ሥልጣን እና ኃላፊነት ወሰን መሠረት ግዴታቸውን ሊወጡ እና የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ያለባቸውን ዕዳ ማጠናቀቃቸውን አረጋግጠው ለቀጣይ ከፍተኛ ትምህርት መቀበል አለባቸው፡፡

29. ሆኖም ግን በኦዲቱ ወቅት መረጃቸው በናሙና ከታዩ ተቋማት ውስጥ ግዴታቸውን በክፍያ ሳይወጡ በጎንደር ዩኒቨርስቲ 6፣ በባህርዳር ዩኒቨርስቲ 10 ፣ በሀዋሣ ዩንቨርስቲ 5 እና በዲላ ዩኒቨርስቲ 7 ተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት ዕዳን ስለማጠናቀቃቸው ሳይረጋገጥ እንዲሁም የስፖንሰር ሺፕ ደብዳቤ እና ኦፊሻል ትራንስክሪፕት ሣያስዙ ለሁለተኛ ዲግሪ ቀጥለው በመማር ላይ የሚገኙ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

30. በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የወጪ መጋራት ደንብ ከወጣ በኋላ 1515 የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ካለምንም ክፍያ እና አገልግሎት ዋናውን የትምህርት ማስረጃ ወስደው ተገኝተዋል፡፡ ከነኝህም ውስጥ 147ቱ የጤና ተመራቂዎች ናቸው፡፡

31. በዚሁ ጉዳይ ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ በተቋማት ላይ ከደንብ እና መመሪያ ውጪ የተሰሩ ግድፈቶች ለወደፊቱ የሚስተካከሉበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ሂሣብን ለመሰብሰብ የዘረጋውን የአሠራር ሥርዓት በተመለከተ፤

32. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን በደንብ ቁጥር 154/2000 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት ከተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት ሂሣብን ለመሰብሰብ የክትትል ሥራ ሊሠራ ይገባል፡፡

33. ለወጪ መጋራት በወጣው ደንብ ቁጥር 154/2000 የወጪ መጋራት ከማንኛውም ተጠቃሚ በ15 ዓመት ውስጥ ተከፈሎ ማለቅ እንዳለበት፣ በግል ከተሰማራ ተጠቃሚ ከዓመታዊ የገቢ ግብር ጋር እንደሚሰበሰብ እንዲሁም ተቀጥሮ ከሚሰራ ተጠቃሚ ከወር ደመወዙ 10% እየተቀነሰ መሰብሰብ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ሆኖም ግን በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ባለሥልጣን መ/ቤቱ ተጠቃሚዎች እና አሰሪ ድርጅቶች የወጪ መጋራት ክፍያን ለመፈፀም በራሳቸው ፍላጎት ካልቀረቡ እና ክፍያ ካልፈፀሙ በስተቀር ክፍያውን ለመሰብሰብ የክትትል ሥራ እንደማይሰራ ነው፡፡

34. በኦዲቱ ወቅት በሰርቬይ እና በአካል ከታዩ 41 አሠሪ ድርጅቶች ውስጥ 7 (17%) ድርጅቶች የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባዘጋጀው የወጪ መጋራት አንድ ሴሚናር ላይ እንደተሳተፉ እና የተቀሩት 34 (83%) ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር በወጪ መጋራት ዙሪያ ምንም ዓይነት መደበኛ ግንኙነት እንደሌላቸው ታውቋል፡፡

35. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በዚህ ዙሪያ ተጠይቆ በደንቡ ውስጥ የአሠራር ሥርዓት ቢቀመጥም መ/ቤቱ የክትትል እና የማስተዋወቅ ሥራ በሚፈለገው መጠን እንዳልሰራ ነገር ግን ወደፊት በስፋት ለመስራት ዕቅድ እንደያዘ ገልጸዋል፡፡

36. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የክትትል እና የማስተዋወቅ ሥራ ባለመስራቱ የወጪ መጋራት ሂሣብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ በሆነ መልኩ እንዳይሰበሰብ አድርጓል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተሰብሳቢ ሂሣብ ስሌት፣ አሰባሰብ እና ፈሠስ አደራረግን በተመለከተ፤

37. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን በቅርንጫፍ መ/ቤቶች፣ በተቋማት፣ ውክልና በሰጣቸው የክልል ከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች የወጪ መጋራት ክፍያ መሰብሰቡን እና ፈሰስ መደረጉን በየ6 ወሩ መከታተል እንዲሁም ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓትን በተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) ሊኖረው ይገባል፡፡

38. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት የመግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) የሌለው ሲሆን የወጪ መጋራት ክፍያ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶም በቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና ውክልና በሰጣቸው ከተማ/ክልል ፋይናንስ ቢሮዎች የወጪ መጋራት ክፍያ መሰብሰቡን እና ፈሠስ መደረጉን አይከታተልም፡፡ ፈሠስ የሚያደርጉለትን እና የማያደርጉለትን ክልሎችም አልያዘም፡፡

39. ይህንንም በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት ከታዩ ክልሎች ውስጥ በኦሮሚያ ክልል የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በክልሉ ካሉ ገቢ ሰብሳቢ ቢሮዎች እስከ 2002 ድረስ ከወጪ መጋራት የሰበሰበውን ብር 4,004,039.34 /አራት ሚሊዮን አራት ሺህ ሠላሣ ዘጠኝ ብር ከሠላሣ አራት ሣንቲም/ እንዲሁም በአዲስ አበባ መስተዳደር የገንዘብ እና

ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በክልሉ እስከ 2002 ከወጪ መጋራት የሰበሰበውን ብር 578,676. /አምስት መቶ ሠባ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሠባ ስድስት ብር/ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ፈሠስ ሳይደረጉ እንደየራሣቸው ክልል ገቢ በመቁጠር ተጠቅመውበት የተገኘ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ መስተዳደር በሥሩ ካሉ ክፍለ ከተሞች እና ሴክተር መ/ቤቶች ለ4 ዓመት የሰበሰበውን የወጪ መጋራት ክፍያ ብር 1,450,681. /አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሀምሣ ሺህ ስድስት መቶ ሠማንያ አንድ ብር/ ፈሠስ የሚያደርግበትን የባንክ ሂሣብ ቁጥር ባለማወቁ ገንዘቡ ሥራ ላይ ሳይውል እና ፈሠስ ሳይደረግ አስተዳደሩ በአደራ ሂሣብ ይዞት ተገኝቷል፡፡

40. የአማራ ክልል ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በክልሉ ካሉ ወረዳዎች እና ዞኖች ከ1998 ጀምሮ የሰበሰበውን የወጪ መጋራት ሂሣብ ለአንድ ዓመት በተከፋይ ሂሣብ (Payable) መዝግቦ የነበረ ቢሆንም ከ1999 ጀምሮ በየደረጃው ካሉ ገቢ ሰብሳቢ ቢሮዎች፣ ወረዳዎችና ዞኖች ለሚሰበስበው የወጪ መጋራት ክፍያ ምንም ዓይነት የሂሣብ ምዝገባ ሳያካሂድ እና በፋይናንስ ሪፖርቱ ውስጥም ሳያሳይ ተገኝቷል፡፡ በባንክ ሂሳብ ማስታወቂያው መሠረት በክልሉ እስከ 2002 ድረስ 4,499,175. ብር /አራት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሠባ አምስት ብር/ ተሰብስቦ ገንዘቡ ሥራ ላይ ሳይውል እና ፈሠስ ሳይደረግ በአደራ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

41. ከዚህም በተጨማሪ በኦዲት ወቅት ከታዩ ተቋማት ውስጥ አዳማ ዩኒቨርስቲ ከቅድሚያ ክፍያ እና ከወጪ መጋራት ተጠቃሚ ሠራተኞች የሰበሰበውን ብር 92,660.07 /ዘጠና ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ስልሣ ብር ከሠባት ሣንቲም/ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ፈሠስ ለማድረግ የባንክ ሂሣብ ቁጥርን ባለማወቁ በሂሣብ መደብ 5002 በአደራ ይዞት የተገኘ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በተመሣሣይ ከቅድሚያ ክፍያ እና ከወጪ መጋራት ሠራተኞቹ የሰበሰበውን ብር 225,017.25 /ሁለት መቶ ሃያ አምስት ሺህ አስራሰባት ብር ከሃያ አምስት ሣንቲም/ ለወጪ መጋራት ከተመደበው የሂሣብ መደብ ውጪ በሌላ ተከፋይ ሂሣብ መደብ ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሠስ አድርጎ ተገኝቷል፡፡

42. ባለሥልጣኑ በዚህ ዙሪያ ተጠይቆ ክልሎች ፈሠስ ያደረጉትን የወጪ መጋራት ሂሣብ እንዲያሳውቁት በደብዳቤ ቢጠይቅም ምላሽ እንዳላገኘ እና ክልሎች ፈሠስ ስለማድረጋቸው ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የመረጃ እጥረት እንዳለበት ገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን የሚመለከቱ መረጃዎች በዳታ ቤዝ የሚይዝ መሆኑን በተመለከተ፣

43. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን እና ቀጣሪ /አሠሪ/ ድርጅቶችን መረጃ በዳታ ቤዝ አጠናክሮ መያዝ እንዲሁም ከእያንዳንዱ ተጠቃሚ የሚፈለገውን የወጪ መጋራት ክፍያ በተጠየቀ ጊዜ ለተጠቃሚዎች እና ቀጣሪዎች ማሳወቅ አለበት፡፡

44. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ባለሥልጣኑ የወጪ መጋራት ክፍያን የፈፀሙ/እየፈፀሙ ያሉ ተጠቃሚዎችን፣ የአሠሪ ድርጅቶች፣ እንዲሁም የተመራቂ ተማሪዎችን ዝርዝር መረጃ በተሟላ ሁኔታ በዳታ ቤዝ ይዞ አልተገኘም፡፡ በሀገሪቱ ካሉት 22 ተቋማት እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ ያስመረቋቸውን ተጠቃሚዎች ዝርዝር መረጃ በተሟላ ሁኔታ ለባለሥልጣኑ የላኩት 7ቱ ብቻ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

45. በዚህም ምክንያት ግዴታቸውን በማይወጡ አሠሪ ድርጅቶች እና ተጠቃሚዎች ላይ የክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓቱ እንዳይጠናከር እና በፍጥነት እየጨመረ ያለውን ተጠቃሚ መረጃ በዳታ ቤዝ ማደራጀት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ በተጨማሪም በባለሥልጣኑ የተጠቃሚ ተመራቂዎች ዝርዝር በተሟላ ሁኔታ ባለመያዙ ከአሠሪ ድርጅቶች እና ተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት መጠን እና ወርሃዊ ክፍያን በተመለከተ ጥያቄ በሚቀርብለት ጊዜ የተሟላ መረጃ ለመስጠት አስቸጋሪ ሆኖበታል፡፡

46. በዚህ ዙሪያ ባለሥልጣኑ ተጠይቆ እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ የተጠቃሚዎችን ዝርዝር ለመያዝ የሚያስችል ቴክኖሎጂ ያልነበረው መሆኑን፣ ወደፊት ግን ለዚሁ የሚረዳ ሶፍትዌር (Software) እያዘጋጀ እንደሆነ ገልጿል፡፡

ከወጪ መጋራት ተጠቃሚ የወር ደመወዝ አሠሪ ድርጅቶች 10% (1/3ኛ) ተቀናሽ ማድረጋቸውን እና በወቅቱ ፈሠስ ማድረጋቸውን በተመለከተ፤

47. አሠሪ ድርጅቶች የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚ ከሆኑ ሠራተኞቻቸው ደመወዝ በየወሩ 10 በመቶ (1/3ኛ) እየቀነሱ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን መ/ቤት ገቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

48. በናሙና ተመርጠው ኦዲት የተደረጉ 3 ሚኒስቴር መ/ቤቶች በጠቅላላ የወጪ መጋራት ተጠቃሚ ከሆኑ ሠራተኞቻቸው በደንቡ መሠረት ከደመወዛቸወ 10% (1/3ኛ) ተቀናሽ አድርገው ለባሥልጣን መ/ቤቱ ገቢ እንደማያደርጉ አረጋግጠናል፡፡

49. ከነዚሁ መ/ቤቶች ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን የመከታተል እና የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው ትምህርት ሚኒስቴርም የወጪ መጋራት ከሚመለከታቸው ከሠራተኞቹ ደመወዝ የወጪ መጋራት ክፍያ ተቀናሽ የማያደርግ ሲሆን፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የወጪ መጋራት ክፍያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ባለመደረጉ እና ሠራተኞቹ እንዳይለቁ በሚል ከወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የሰበሰበውን ክፍያ ሂሣብ መልሶ ለተጠቃሚዎቹ ተመላሽ ማድረጉ ተረጋግጧል፡፡

50. አሠሪ ድርጅቶች በዚህ ዙሪያ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የግንዛቤ እጥረትን፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ያለመደረጉን እና የሠራተኞች ሥራ መልቀቅን በምክንያትነት ጠቅሰዋል፡፡

51. አሠሪ ድርጅቶች ከተጠቃሚዎች የሚፈለግባቸውን ክፍያ ተቀናሽ አለማድረጋቸው ከወጪ መጋራት የሚገኘውን ገቢ በአግባቡ እንዳይሰበሰብ እና የወጪ መጋራት ዓላማ ተግባራዊ እንዳይሆን አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

ለ. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን ተፈፃሚ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት እና ወጥ በሆነ መልኩ የሚሰሩ መሆኑ እንዲሁም ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋታቸውን በተመለከተ፤

የትምህርት ሚኒስቴር ደንብ ቁጥር 154/2000 ለማስፈጸም ያወጣውን መመሪያ ለባለድርሻ አካላት የሚያሰራጭበትን መንገድ በተመለከተ፤

52. የትምህርት ሚኒስቴር ለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ደንብ ቁጥር 154/2000 የአፈፃፀም መመሪያ ሊያወጣ እና ፈጣን የአላላክ ዘዴን በመጠቀም ለባለድርሻ አካላት ወዲያውኑ ሊልክ ይገባል፡፡

53. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጪ መጋራት ደንብ ቁጥር 154/2000 የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣው ከዘጠኝ ወር በኋላ ግንቦት 12/2001 ዓ.ም. ሲሆን ለተቋማት የተላከው 48 ቀናት ዘግይቶ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለወጪ መጋራት በወጣው ደንብ እና በአፈፃፀም መመሪያ መሀል ለነበረው የዘጠኝ ወር የጊዜ ክፍተት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መመሪያ ባለመተላለፉ ምክንያት በናሙና ከታዩት ስድስት /6/ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የወጪ መጋራት ፅዳቸውን ሳይፈጽሙ ዋናውን ዲግሪያቸውን የወሰዱ ከሀዋሣ ዩኒቨርስቲ 11፣ ከአዳማ ዩኒቨርስቲ 8 እንዲሁም ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ 22 ተጠቃሚዎች የተገኙ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በትምህርት ሂደት ለሚወጡ የላብራቶሪ ኬሚካሎች ተመን መመሪያ አለማውጣቱ ተረጋግጧል፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተመረቁ እና ያቋረጡ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን እንዲያሳውቁት ስለማድረጉ፤

54. የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየበጀት ዓመቱ የተመረቁ እና ያቋረጡ ተማሪዎችን ዝርዝር እንዲያሳውቁት ሊያደርግ እና ተቋማት የወጪ መጋራት ሂሣብን በየበጀት ዓመቱ አስልተው ሊይዙ ይገባል፡፡

55. ተቋማት በየበጀት ዓመቱ የተመረቁ እና ያቋረጡ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር ለትምህርት ሚኒስቴር እንዲያሳውቁት የማያደርግ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት ከታዩ ተቋማት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከ2001 ዓ.ም. በፊት ያስመረቃቸውን የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የዘጠኝ ወር አገልግሎት በመስጠት

እና ያልተጠቀሙበትን የአንድ ወር እዳ ጨምሮ በማስላት በአጠቃላይ የአሥር ወር ውል ያስገባ እንደነበር ታውቋል፡፡

56. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ተቋማት ውስጥ የሀዋሣ ዩኒቨርስቲ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተመረቁ እና ያቋረጡ ተጠቃሚዎችን ሲልክ በግልባጭ ለትምህርት ሚኒስቴር አለማሣወቁ እንዲሁም ጎንደር ዩኒቨርስቲ ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ የተመረቁ እና ያቋረጡ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝርን መላክ ያቋረጠ መሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

57. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ደንቡ ሥራ ላይ መዋሉን ካለባቸው የመከታተል እና የማረጋገጥ ኃላፊነት አንፃር የሚስተዋሉ ችግሮችን ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን ተፈፃሚነትን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጣቸው ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ መፍጠራቸውን በተመለከተ፤

58. የወጪ መጋራትን ለማስፈፀም ሥልጣን እና ኃላፊነት የተሰጣቸው ባለድርሻ አካላት በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት አፈፃፀም እና በአፈፃፀሙ ዙሪያ ስለሚያጋጥሙ ችግሮች የመወያያ መድረክ በመፍጠር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሊሰሩ ይገባል፡፡

59. በናሙና ተመርጠሙ ኦዲት የተደረጉት ስድስት ተቋማት ለተጠቃሚዎች ስለወጪ መጋራት የግንዛቤ ማስጨበጫ ማንዋል እንደማያዘጋጁ እንዲሁም ከትምህርት ሚኒስቴር እና ከኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር በወጪ መጋራት ዙሪያ መደበኛ የሆነ የሥራ ግንኙነት እንደሌላቸው ታውቋል፡፡

60. ስለሁኔታው የየተቋማቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለተጠቃሚዎች ስለወጪ መጋራት ግንዛቤ የሚያስጨብጡት በቃል ብቻ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

61. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት የመወያያ መድረክን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተቋማት ጋር እና ከኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር በደብዳቤ እንደሚገናኙ ሆኖም ግን

ወደፊት የጋራ የውይይት መድረክ በመፍጠር ችግሮችን ለመፍታት እንደሚጥሩ ገልጸዋል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚያስተላልፉትን ሪፖርትን በተመለከተ፤

62. ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየትምህርት ዘመኑ ያቋረጡ እና የተመረቁ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ዝርዝርን በተመረቁ በ3 ወራት ውስጥ በአገልግሎት እና ክፍያ ለይተው ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

63. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የባህርዳር፣ አዳማ፣ ሀዋሣ እና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲዎች የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር ከ8 እስከ 24 ወራት አዘግይተው ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚልኩ ሲሆን ጎንደር ዩኒቨርስቲ ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ የተመራቂዎችን ዝርዝር ለባለሥልጣኑ ልኮ የማያውቅ መሆኑን፣ በተመሣሣይም ኦዲቱ ከሸፈናቸው ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ዲላ ዩኒቨርስቲ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣንም ሆነ ለትምህርት ሚኒስቴር ልኮ የማያውቅ መሆኑ፣

64. ከዚህም በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት መረጃቸው ከታዩ 9 ተቋማት ውስጥ የተጠቃሚዎች ዕዳ በአገልግሎት ይሁን በክፍያ ለይተው በተሟላ ሁኔታ የሚልኩ 3 ተቋማት ብቻ መሆናቸው ታውቋል፡፡

65. ይህም የወጪ መጋራት ክፍያን ለማስተባበር እና ለመቆጣጠር ለባለሥልጣኑ እንቅፋት የሚሆን ሲሆን፣ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችም ሆኑ ቀጣሪ አሠሪ ድርጅቶች ክፍያ ለመፈፀም የተጠቃሚዎችን የዕዳ መጠን ባለሥልጣኑን ሲጠይቅ ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሰጠው ውክልና እና በውክልናው መሠረት መሰራቱን በተመለከተ፤

66. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የወጪ መጋራት ክፍያን ለመሰብሰብ ለክልል/ከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች ውክልና መስጠት እና በሰጠው ውክልና

መሠረት ሥራው መተግበሩን የሚከታተልበት፣ የሚቆጣጠርበት እና የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

67. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተሻረው ደንብ ቁጥር 91/95 መሠረት በሰጠው ውክልና ውስጥ ስለወጪ መጋራት ሂሣብ አሰባሰብ፣ ፈሰስ አደራረግ፣ የባንክ ሂሣብ ቁጥር እና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት አቀራረብ እንዲሁም ውክልና የሰጣቸው ድርጅቶች መስጠት ስለሚችሉት ማስረጃ የተገለፀ ነገር የሌለ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት ከታዩ ሁሉም የክልል ከተማ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ጋር በወጪ መጋራት ዙሪያ ምንም ዓይነት መደበኛ ግንኙነት የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

68. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ባለሥልጣኑ በተሻረው ደንብ ቁጥር 91/95 መሠረት የሰጠውን ውክልና ባለማሻሻሉ እና ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር መረጃዎች ባለማካተቱ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ገቢ ሰብሳቢ ቢሮዎች ለወጪ መጋራት ከተመደበው የሂሣብ መደብ ውጭ በአምስት የተለያዩ የሂሣብ መደቦች ይዘው የተገኙ ሲሆን ከወጪ መጋራት የሰበሰቡትን ሂሣብ እንደራሳቸው ክልል ገቢ የተጠቀሙ እና ፈሠስ ሳያደርጉ በአደራ የያዙ የክልል የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ተገኝተዋል፡፡

በባለሥልጣኑ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በዚህ ዙሪያ ተጠይቀው የሰጡት መልስ በውክልናው ላይ ወካይ እና ተወካይ ያለባቸው ግዴታና ኃላፊነት በግልጽ ሰፍሮ ወካይ እና ተወካይ ያልተፈራረሙበት በመሆኑ ችግሮቹ ያጋጠሙ መሆኑን፣ ወደፊት ግን ውክልናውን ለማሻሻል እና መደበኛ የመወያያ መድረክ ለመፍጠር በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መስጠቱን በተመለከተ፤

69. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለእያንዳንዱ የወጪ መጋራት ተጠቃሚ የግብር መለያ ቁጥር ሊሰጥ ይገባል፡፡

70. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ በ2002 ዓ.ም. በተቋማት ውስጥ የሚገኙ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን አሻራ የሰበሰበ ቢሆንም ከ2002 ዓ.ም. በፊት ለነበሩ ተጠቃሚዎችም ሆነ በ2002 አሻራ ለሰጡ ተማሪዎች የግብር መለያ ቁጥር አልሰጠም፡፡

71. የግብር መለያ ቁጥር ለወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ባለመስጠቱ ስለተጠቃሚዎች ብዛት፣ ተጠቃሚዎች ስለአለባቸውና ስለከፈሉት የዕዳ መጠን፣ እንዲሁም ክፍያ ስለአቋረጡና ክፍያ ስለአልጀመሩ ተጠቃሚዎች በባለሥልጣኑ መረጃ የሌለው ሲሆን ይህም የቁጥጥር ሥራው የላላ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል፡፡

72. የሚመለከታቸው የባለሥልጣኑ የሥራ ኃላፊዎች በዚህ ዙሪያ ተጠይቀው በ2002 ዓ.ም. ከ149,820 ተማሪዎች አሻራ እንደሰበሰቡ ነገር ግን የማተም ሥራ ጊዜ ስለፈጀ የግብር መለያ ቁጥር እንዳልሰጡ ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በተመለከተ ለባለድርሻ አካላት ስለሚያስተላልፈው መረጃ፤

73. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከተቋማት የሚመጣለትን የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ዝርዝር ለቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና ውክልና ለሰጣቸው ክልል/ከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች ማሰራጨት እንዲሁም ለተቋማት ውክልና የሰጣቸውን የክልል/ከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች ዝርዝር ማሳወቅ አለበት፡፡

74. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን በኦዲቱ ወቅት ለታዩት ለሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ክፍያን እንዲሰበስቡ ውክልና የሰጣቸውን የክልል/ከተማ ፋይናንስ አስተዳደር ቢሮዎችን ዝርዝር የማያሳውቅ መሆኑ፣ ለባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ውክልና ለሰጣቸው የክልል/ከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች በሙሉ ከተቋማት የተላከለትን የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር መረጃ የወጪ መጋራት ከተጀመረበት ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ኦዲቱ እስከ ተከናወነበት 2003 ዓ.ም. ድረስ ልኮ የማያውቅ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

75. ባለሥልጣኑ ለተቋማት ውክልና የሰጣቸውን ቢሮዎች ባለማሳወቁ እና ተቋማት ውክልና ስለተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ ቢሮዎች መረጃ ስለሌላቸው በተለያዩ ደረጃ ካሉ ገቢ ሰብሳቢ ቢሮዎች እና ባለሥልጣናት የሚመጣላቸውን የተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት ክፍያ ምስክር ወረቀት /ደብዳቤ/ አንቀበልም በማለታቸው ተጠቃሚዎች ወደ ዋናው ባለሥልጣን እና የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመሄድ መረጃውን እንደገና እንዲያረጋግጡ በተቋማት ይጠየቃሉ፡፡ ይህም ከፍተኛ እንግልት እና ወጪ በተጠቃሚዎች ላይ ያስከትላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ባለሥልጣኑ ለቅርንጫፍ

መ/ቤቶች እና ውክልና ለሰጣቸው ቢሮዎች የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር መረጃ ባለማሰራጨቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ውክልና በተሰጣቸው ቢሮዎች ክፍያ ለመፈፀም የሚመጡ ተጠቃሚዎች ወደ ተቋማት እና ወደ ዋናው ባለሥልጣን መ/ቤት ሳይመላለሱ በመጡበት ወቅት እንዳይስተናገዱ እንቅፋት ሆኗል፡፡

76. የሚመለከታቸው የባለሥልጣኑ የሥራ ኃላፊዎች በዚህ ዙሪያ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለተቋማት መረጃውን ያላስተላለፉት ለክልሎች የተሰጠው ውክልና ክሊራንስ መስጠትን የማያካትት ስለሆነ መሆኑን፣ ነገር ግን የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር በተሟላ ሁኔታ እንዳላሰራጨ እና ወደፊት ግን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተደራጅተው እንዲሰራጩ ለማድረግ እየሰሩ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚን የሚቀጥሩ አሰሪ ድርጅቶች ተጠቃሚዎች ከተቋማት ጋር የገቡትን ውል የሚያሳይ ማስረጃ መጠየቃቸውን እና በየ3 ወሩ ዝርዝራቸውን ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሪፖርት ማድረጋቸውን በተመለከተ፤

77. አሰሪ ድርጅቶች የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ሲቀጥሩ ተቀጣሪዎቹ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር የገቡትን ውል በመጠየቅ በየ3 ወሩ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የከፍተኛ ወጪ መጋራት የሚመለከታቸውን ተቀጣሪዎች ዝርዝር ሊያሳውቁ ይገባል፡፡

78. በናሙና ተመርጠው ኦዲት ከተደረጉ 11 አሰሪ ድርጅቶች ውስጥ 7ቱ (64%) እንዲሁም በሰርቬይ ቃለ-መጠይቅ ከተበተነላቸው 22 አሰሪ ድርጅቶች ውስጥ 10 (45%) በደንቡ እና የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ መሠረት የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚን በሚቀጥሩበት ጊዜ ከተጠቃሚው፣ ከተመረቀበት ተቋም ወይም ከባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚፈለግበትን የክፍያ ሂሳብ /የአገልግሎት/ ጊዜ የሚገልጽ ማስረጃ የማይጠይቁ መሆኑን፣ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ኦዲት ከተደረጉ 24 አሰሪ ድርጅቶች 24 (100%)፣ በሰርቬይ ቃለ-መጠይቅ ከተላከላቸው እና ምላሽ ከሰጡ 22 አሰሪ ድርጅቶች 19 (95%) በደንቡ እና የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ መሠረት የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚ ሠራተኞቻቸውን ዝርዝር በየ3 ወሩ ለባለሥልጣን መ/ቤት የማያሳውቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

79. ይህ ሊሆን የቻለው አዋጁና ደንቡን እንዲያስፈጽሙ የመከታተል፣ የመቆጣጠር እና ተግባራዊ መሆኑን የማረጋገጥ ሥልጣን እና ኃላፊነት የተሰጣቸው የትምህርት ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለደንቡ ተፈፃሚነት በቂ ትኩረት ሰጥተው በሰው ኃይል የተሞላ አደረጃጀት ፈጥረው የቁጥጥር፣ የክትትል እና ግንዛቤ የመፍጠሩን ሥራ በበቂ ሁኔታ ባለመሰራታቸው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ክፍል ሦስት
የመደምደሚያ ሀሣቦች

የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚዎች መንግሥት ለትምህርትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያወጣውን ወጪ የሚጋሩበትን ሥርዓት ለመዘርጋት እና ለማስፈፀም የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፣ ከክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በመንግሥት የሚወጡ ደንቦች በአግባቡ ተፈፃሚና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ አላማ አንፃር የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት አፈፃፀም እና ውጤታማነት በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

80. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን ተፈፃሚነት የመከታተል፣ የመቆጣጠር እና ተግባራዊነቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ደንቡን በበቂ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተፈፃሚ ማድረግ የሚያስችል በሰው ኃይል የተሟላ አደረጃጀት ባለመፍጠራቸው በደንቡ የተሰጣቸውን ሥልጣን እና ኃላፊነት እንዳይወጡ ማድረጉ፣

81. በኦዲቱ በተገኘው መረጃ /ማስረጃ/ መሠረት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከደንብ ቁጥር 154/2000 እና ትምህርት ሚኒስቴር ካወጣው የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 003/2000 ውጪ እየተሰራ ያለ ሥራ መኖሩ እና ይህንንም ለማስተካከል በትምህርት ሚኒስቴር የተወሰደ እርምጃ ባለመኖሩ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚ ሆነው የክፍያ /የአገልግሎት/ ግዴታቸውን ሳይወጡ ዋናውን የትምህርት ማስረጃቸውን የሚወስዱ እና ለቀጣይ ከፍተኛ ትምህርት የሚቀበሉ ተቋማት ያሉ መሆኑ፣

82. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የወጪ መጋራት ክፍያ መሰብሰቡን፣ ፈሠስ መደረጉን እና በሰጠው ውክልና መሠረት ሥራው መተግበሩን ባለመከታተሉ ክልሎች የሰበሰቡትን ገንዘብ እንደየራሳቸው ገቢ ተጠቅመውበት መገኘቱ እንዲሁም ከወጪ መጋራት የሰበሰቡትን ገንዘብ ፈሠስ ሳይደረጉ አስቀምጠው መገኘታቸው፣

83. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከተቋማት እና ውክልና ከሠጣቸው የክልል/ከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች ጋር የተሟላ የመረጃ ልውውጥ ባለመኖሩ ዕዳቸውን ለመወጣት በሚፈልጉ ተጠቃሚዎች ላይ መጉላላት የፈጠረ መሆኑ፣

84. ለወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የግብር መለያ ቁጥር አለመሰጠቱ ባለሥልጣኑ ተጠቃሚዎች ዕዳቸውን እንዲወጡ በበቂ ሁኔታ ለመከታተል እና ለማስፈፀም እንዳይችል ምክንያት መሆኑ፣

85. በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት አፈፃፀም ዙሪያ ችግሮች በመለየት እርምጃ ለመውሰድ እና መልካም ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ በሚያስችል መልኩ የትምህርት ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የመወያያ መድረክ ባለመፍጠራቸው የወጪ መጋራት በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ በሆነ መልኩ እንዳይተገበር አስተዋጽኦ ማድረጉ፡፡

86. አሠሪ ድርጅቶች የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚዎች ከተቋማት ጋር የገቡትን ውል /ማስረጃ/ ባለመያዛቸው እና ዝርዝራቸውን በየ3 ወሩ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባለማስተላለፋቸው በአገር አቀፍ ደረጃ ምን ያህል ተጠቃሚዎች ግዴታቸውን እንደተወጡ /እየተወጡ/ እንዳሉ የተሟላ መረጃ እንዳይኖር የሚያደርግ እና እያንዳንዱ ተጠቃሚ ያለበት የክፍያ ሂሣብ /የአገልግሎት/ ግዴታ በወቅቱ እንዳይወጣ ችግር የሚፈጥር መሆኑ፣

87. በአጠቃላይ አፈፃፀሙን እንዲከታተሉ ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ኃላፊነታቸውን በተሟላ ሁኔታ አለመወጣታቸው፣ በቅንጅት አለመስራታቸው እና በመካከላቸው ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለመኖሩ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በትምህርት ሚኒስቴር የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ /ከ1998-2002/ ከወጪ መጋራት ገቢ ይገኛል ተብሎ የተያዘውን ሂሳብ በዘጠና ሁለት በመቶ /92%/ ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተፈፃሚና ውጤታማ ለማድረግ ተገቢ ትኩረት እንዳልተሰጠው ከዚህ መረዳት ይቻላል፡፡

ክፍል አራት
የማሻሻያ ሀሣቦች

88. የወጪ መጋራትን ለማስፈፀም ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው ሁሉም ባለድርሻ አካላት የተሠጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመወጣት በሥራ ስፋታቸው መሠረት የወጪ መጋራትን በአግባቡ ለመወጣት በሚያስችላቸው ሁኔታ አደረጃጀት በመፍጠር እና በቦታው ላይ ተገቢውን የሠው ኃይል በመመደብ ሥራውን በቅልጥፍና ሊሠሩ ይገባል፡፡

89. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዘጋጀው ስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት የወጪ መጋራት መተግበሩን በየበጀት ዓመቱ በሚያዘጋጀው ዕቅድ እና የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ በዝርዝር በማካተት ባልተከናወኑት ተግባራት ላይ ምክንያቱን በጥልቀት በመረዳት የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

90. ትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከደንብ እና መመሪያ ውጭ የሠሩአቸውን ሥራዎች የሚስተካከሉበትን መንገድ ከተቋማት ጋር በጋራ በመሥራት እንዲስተካከሉ ሊያደርግ እና ለወደፊቱ ተመሣሣይ ሁኔታ እንዳይፈጠር በቂ የክትትል እና የቁጥጥር ሥራ ሊሠራ ይገባል፡፡

91. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተጠቃሚዎች ስለአለባቸው ዕዳ፣ ስለከፈሉት የዕዳ መጠን፣ ክፍያ ስለአቋረጡ እንዲሁም ክፍያ ስላልጀመሩ ተጠቃሚዎች መረጃ ለመያዝ እና ለመቆጣጠር ለወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የግብር መለያ ቁጥር ሊሰጥ ይገባል፡፡

92. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለክልል/ከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች በሚሰጠው ውክልና ውስጥ የወጪ መጋራት ሂሣብን የተወከሉት ቢሮዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ ስለክፊያው አሰባሰብ፣ ስለተሰበሰበው ሂሣብ ፈሠስ አደራረግ፣ ፈሠስ ስለሚደረግበት የባንክ ሂሣብ ቁጥር፣ ስለሪፖርት አቀራረብ እና መስጠት ስለሚችሉት የማስረጃ ዓይነት ሊገልጽ እና በውክልናው መሠረት የወጪ መጋራት መሰብሰቡን በሪፖርት ሊከታተል ይገባል፡፡

93. የወጪ መጋራት ክፍያ በአግባቡ እና ወጥ በሆነ መልኩ እንዲሰበሰብ የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ መፍጠር፣ በባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥር ላሉ አሠሪ ድርጅቶች ደብዳቤ በመበተን እና በግል ሥራ ላይ ካሉ ተጠቃሚዎች ከገቢ ግብር ጋር አብሮ በመሰብሰብ የወጪ መጋራት ክፍያ በተገቢው ሁኔታ መሰብሰቡን እና ፈሠስ መደረጉን መከታተል እና መቆጣጠር ይገባዋል፡፡

94. የትምህርት ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የወጪ መጋራትን ለመቆጣጠር፣ በወጪ መጋራት ዙሪያ ችግሮችን ለመለየትና እና ለችግሮቹ መፍትሄ ለመስጠት የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት በተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) ሊፈራረሙ እና ባለሥልጣኑ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ ተቋማት እና ውክልና በሰጣቸው ከተማ/ክልል ፋይናንስ ቢሮዎች የወጪ መጋራት ክፍያ መሰብሰቡን እና ፈሠስ መደረጉን በየ6 ወሩ በሪፖርት ሊከታተል ይገባዋል፡፡

95. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች እና ቀጣሪ /አሠሪ/ ድርጅቶች ለክፍያ በመጡበት ጊዜ ለማስተናገድ እንዲያስችለው የወጪ መጋራት ተጠቃሚ ተመራቂዎችን ዝርዝር በአገልግሎት እና በክፍያ ለይተው በተመረቁ በ3 ወር ውስጥ ለባለሥልጣኑ መላክ እንዲሁም ባለሥልጣኑ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን እና ቀጣሪ /አሠሪ/ ድርጅቶችን ዝርዝር መረጃ በዳታ ቤዝ መያዝ እና በተጠየቀ ጊዜ ለተጠቃሚዎች እና ቀጣሪዎች ማሣወቅ አለበት፡፡

96. ተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት ክፍያን በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በተወከሉ ገቢ ሰብሳቢ ቢሮዎች ሲፈፀሙ እንዳይጉላሉ እንዲሁም ውክልና የተሰጣቸው ቢሮዎች እና የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተጠቃሚዎች ወደ የቢሮዎቻቸው ክፍያ ለመፈፀም በሚመጡበት ጊዜ ወዲያውኑ ማስተናገድ እንዲችሉ የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስለተጠቃሚዎች እና ውክልና ስለሰጣቸው ቢሮዎች መረጃ ሊያስተላልፍላቸው ይገባል፡፡

97. አሥሪ ድርጅቶች መሰብሰብ ያለበት የወጪ መጋራት ክፍያ እንዲሰበሰብ እና የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን የወጪ መጋራት ክፍያን ለመከታተል መረጃ ለማጠናቀር እንዲያመቸው የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ሲቀጥሩ ከተቋማት የተቀበሉትን ውል ጠይቆ በመቀበል፣ የወጪ መጋራት የሚመለከታቸውን ተቀጣሪዎችን ዝርዝር በየ3 ወሩ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማሣወቅ እና ከቀጠሯቸው ተጠቃሚዎች ደመወዝ በየወሩ 10% (1/3ኛ) እየቀነሱ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

98. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለደንቡ ተፈፃሚነት የሚያወጣቸው መመሪያዎች ለባለድርሻ አካላት በወቅቱ ደርሰው ተግባራዊ እንዲያደረጉ እና በመዘግየታቸው የአፈፃፀም ክፍተት እንዳያጋጥም ፈጣን የአላላክ ዘዴን በመጠቀም ወዲያውኑ ሊያሳውቅ እንዲሁም በአፈፃፀም መመሪያው ላይ በግልጽ ላልተቀመጡ አሠራሮች ተጨማሪ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይገባል፡፡

99. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየዓመቱ የሚያስመርቋቸውን እና ያቋረጡ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር እንዲያሣውቁት በማድረግ በወቅቱ በማያሣውቁት ላይ ክትትል በማድረግ፣ ከተቋማት እና ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር በመወያየት ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ክፍያ ያልፈፀሙ ተጠቃሚዎች ትክክለኛ ሂሣብ ተሰልቶ እንዲከፍሉ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

100. ከየተቋማቱ የሚመረቁ ተጠቃሚዎች ስለወጪ መጋራት አንድ ዓይነት ግንዛቤ እንዲያገኙ የአፈፃፀም መመሪያውን መሠረት በማድረግ ግንዛቤ ለመስጠት ተቋማት ማንዋል፣ ብሮሽር እና በራሪ ወረቀቶችን በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች ኦረንቴሽን መስጠት እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ የመወያያ መድረክ ፈጥሮ የምክር፣ የድጋፍ እና የግንዛቤ መፍጠር ሥራ ለባለድርሻ አካላት ሊሠጥ ይገባል፡፡

አባሪ 1

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

የኦዲት ጭብጦች (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርት (Evaluative Criteria)
1.የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በተመለከተ የወጡ አዋጆች እና ደንቦች ተፈጻሚ እንዲያደርጉ ስልጣንና ኋላፊነት የተሰጣቸው ባለድርሻ አካላት የደንቡን ተግባራዊነት ለማረጋገጥ ውጤታማነቱን ለመከታተል ና ለመቆጣጠር የሚያስችል አደረጃጀት እና የአሰራር ሥርዓት የዘረጉ መሆኑን ማረጋገጥ፤	1.የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በተመለከተ የወጡ አዋጆችንና ደንቦችን ተፈፃሚነትን ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር እና መተግበሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል አደረጃጀት ሊኖረው ይገባል፡፡
1.1 ትምህርት ሚኒስቴር በአዋጅ እና በደንቡ መሠረት የተሠጠውን ኃላፊነት በብቃት እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እየተወጣ መሆኑን ማረጋገጥ	2.ሚኒቴር መ/ቤቱ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በተመለከተ የወጡ አዋጆችንና ደንቦችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአፈፃፀም መመሪያ ሊያወጣ ይገባል፡፡
	3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየጊዜው በሚያዘጋጀው የስትራቴጂክ እና ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ዙሪያ የሚሰራውን ስራ ሊያካትት ይገባል፡፡
	4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየጊዜው በሚያዘጋጀው የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ዙሪያ የሚሰራውን ስራ እና በሪፖርቱ መሠረት ለሚታዩ ክፍተቶች እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
	5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየበጀት ዓመቱ የተመረቁ እና ያቋረጡ ተማሪዎችን ዝርዝር እንዲያሳውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡
1.2 በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የሚፈለግባቸውን የክፍያ ዕዳ አሰባሰብ ለማስፈፀም፣ ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል አሰራር መኖሩን ማረጋገጥ፡፡	6. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጪ መጋራት ክፍያን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችል ራሱን የቻለ የሥራ ክፍል ማደራጀት ይገባዋል፡፡
	7. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከእያንዳንዱ ተጠቃሚ የሚፈለገውን የወጪ መጋራት መጠንና ወርሃዊ ክፍያውን ጭምር በተጠየቀ ጊዜ ለተጠቃሚዎች እና ለቀጣሪዎች ማሳወቅ የሚያስችለው የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡
	8. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጪ መጋራት ክፍያን የፈፀሙ/እየፈፀሙ ያሉ ተጠቃሚዎችን እና አሠሪ ድርጅቶችን መረጃ (የተጠቃሚዎችን ዝርዝር፣ ቀሪ የዕዳ መጠን...) በዳታ ቤዝ/ዳታ አያያዝ ስርአት አጠናክሮ መያዝ አለበት፡፡
	9. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቅርንጫፍ መ/ቤቶች፣ በተቋማት፣ ውክልና በሰጣቸው የክልል እና ከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች የወጪ መጋራት ክፍያ መሰበሰቡን እና ፈሰስ መደረጉን በየ6 ወሩ ሊከታተል ይገባል፡፡
	10. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በክልል መ/ቤቶች ውስጥ ከሚቀጠሩ ተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት ክፍያን ለመሰብሰብ ለክልልና ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮዎች ውክልና መስጠት ይገባዋል፡፡

የኦዲት ጭብጦች (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርት (Evaluative Criteria)
	11.የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለክልል/ከተማ ፋይናንስ አስተዳደር ውክልና ሲሰጥ ሀላፊነታቸውን (የወጪ መጋራት ሂሳብ አሰባሰብ፣ ፈሰስ እና ሪፖርት አደራረግ) በውክልናው ሠነድ ውስጥ ሊያካትት ይገባል፡፡
	12.የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለክልል/ከተማ ፋይናንስ አስተዳደር በሰጠው ውክልና መሠረት ሥራው መተግበሩን የሚከታተልበት፣ የማቆጣጠርበትና የሚያረጋግጥበት ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡
	13.የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በደንብ ቁጥር 154/2000 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት ከተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት ሂሳብ ለመሰብሰብ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት መሰብሰብ አለበት፡፡
	14. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለእያንዳንዱ የወጪ መጋራት ተጠቃሚ የግብር መለያ ቁጥር ሊሰጥ ይገባል፡፡
	15.የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በየዓመቱ በሚያዘጋጀው እቅድ እና የእቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ የወጪ መጋራትን ማካተት አለበት፡፡
1.3 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአዋጅ እና በደንቡ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በብቃት እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እየተወጡ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡	16.ተቋማት ለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች በየትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን በተመለከተ ማንዋል፣ ብሮሸር . . . ወዘተ በማዘጋጀት ግንዛቤ ሊያስጨብጣቸው ይገባል፡፡
	17.ተቋማት የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን የሚከታተል የሥራ ክፍል ሊያደራጁ ይገባል፡፡
	18. ተቋማት በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለተመረቁ እና ላቋረጡ ተማሪዎች በየበጀት ዓመቱ የተጠቀሙትን የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ሂሳብን አስልቶ ሊይዙ ይገባል፡፡
	19. ተቋማት በደንብ ቁጥር 154/2000 መሠረት በመንግሥት ተመድበው የሚገቡትን ተማሪዎች ብቻ በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ሊያሳትፉ ይገባል፡፡
	20. ተቋማት በደንቡ በተሰጣቸው የስልጣንና ሀላፊነት ወሰን መሠረት ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡
	21. ተቋማት የወጪ መጋራት ክፍያን በገንዘብ ወይም በአገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበትን ተጠቃሚ ክፍያውን ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እንዲሁም አገልግሎቱን አገልግሎት ሲሰጥበት ከነበረው ተቋም ማጠናቀቁን አረጋግጦ ለቀጣይ ከፍተኛ ትምህርት መቀበል አለበት፡፡
1.4 ከመንግስት ተቋማት ተመርቀው የሚወጡ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ቀጥረው የሚያሰሩ አሰሪ ድርጅቶች በደንቡ መሰረት የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት እየተወጡ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡	22. አሰሪ ድርጅቶች የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚ ከሆኑ ሰራተኞቻቸው በየወሩ 10 በመቶ /የደመወዛቸውን 1/3ኛ የማይበልጥ እየቀነሱ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ገቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
	23. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚን የሚቀጥር አሰሪ ድርጅት ተጠቃሚው ከተመረቀበት ተቋም ወይም ከገቢዎች ባለሥልጣን ግለሰቡ የሚፈለግበትን ክፍያ መጠን/ሂሳብ የሚገልፅ ማስረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡
	24. አሰሪ ድርጅቶች በየ3 ወሩ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚ የሆኑ በድርጅታቸው የተቀጠሩ የሠራተኞች ዝርዝር ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሊያሳውቁ ይገባል፡፡
2.የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ደንብ ተፈጻሚ የሚያደርጉ ባለድርሻ	25. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያወጣቸውን የአፈፃፀም መመሪያዎች ለባለድርሻ አካላት ፈጣን የአላላክ ዘዴን በመጠቀም (ኢሜል፣

የኦዲት ጭብጦች (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርት (Evaluative Criteria)
አካላት በቅንጅት የሚሰሩ መሆኑን እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት የዘረጉ ና ተግባራዊ ያደረጉ መሆኑን ማረጋረጥ፡፡	ፖስታ፣ ትራንስፖር ወዘተ...) በአንድ ዓምንት ጊዜ ውስጥ ሊልክ ይገባል፡፡
	26. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር የአሰባሰቡን ሂደት በተመለከተ የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ስምምነት (memorandum of understanding) ሊኖረው ይገባል፡፡
	27. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ በሆነ ሁኔታ (በአመት አንድ ጊዜ) በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት አፈፃፀምና በአፈፃፀሙ ዙሪያ ስለአጋጠሙ ችግሮች መወያያ መድረክ ሊፈጥር ይገባል፡፡
	28. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወጥ በሆነ መልኩ በክፍያና በአገልግሎት ግዴታቸውን መወጣት ያለባቸው ተጠቃሚዎች ሊያሳይ የሚችል የወጪ መጋራት ሪፖርት መላኪያ ቅፅ አዘጋጅቶ ሊልክ ይገባል፡፡
	29. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከተቋማት የሚመጣለትን የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ዝርዝር ለቅርንጫፍ መ/ቤቶችና ለክልል/ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮዎች ከተቋማት በደረሰው በሦስት ቀን ውስጥ ማሰራጨት አለበት፡፡
	30. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጪ መጋራት ክፍያ አሰባሰብ በተገቢው ሁኔታ እንዲፈፀም ለአሰሪ ድርጅቶች፣ ለተጠቃሚዎች እና ውክልና ለሰጣቸው ቢሮዎች የምክር፣ ድጋፍና የግንዛቤ መፍጠር ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡
	31. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ውክልና የሰጣቸውን የክልል/ከተማ ፋይናንስ አስተዳደር ቢሮዎችን ዝርዝር ለተቋማት ማሳወቅ አለበት፡፡
	32. ተቋማት ከተጠቃሚዎች የሚቀበሉትን የወጪ መጋራት ቅድሚያ ክፍያ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማስተላለፍ አለባቸው፡፡
	33. ተቋማት በየትምህርት ዘመኑ ያቋረጡ እና የተመረቁ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ዝርዝርን በተመረቁ በ3 ወር ውስጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ግምሩክ ባለስልጣን ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡
	34. ተቋማት በየትምህርት ዘመኑ መጨረሻ በትምህርት ዘመኑ ያቋረጡ እና የተመረቁ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ዝርዝርን ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአገልግሎትና በክፍያ ለይተው ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

አባሪ 2

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች እና በአሰሪ ድርጅቶች የተሰበሰበውን መረጃ መተንተን (Data Analysis)

በዚህ ክፍል በኦዲቱ ወቅት ከ22 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በናሙና ከተመረጡት ስድስት ተቋማት፣ በኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን አራት ቅ/ጽ/ቤቶች እና ከአራት የክልል/የከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች እንዲሁም በአካል ከታዩት 24 መ/ቤቶች እና መጠይቅ ከተበተነላቸው 60 አሰሪ ድርጅቶች ስለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት አፈፃፀም እና ውጤታማነት በአካል በመገኘት፣ ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ማስረጃዎችን በማሰባሰብ የተሠራ የመረጃ ትንተና (Data Analysis) ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 1.1 ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተገኘ መረጃ ትንተና

ተ.ቁ.	መግለጫ	በኦዲቱ ምላሽ የሰጡ ተቋማት ብዛት እና በመቶኛ			
		አዎ	በመቶኛ % age	አይደለም	በመቶኛ % age
1	ተቋሙ በደንቡ መሠረት ስለወጪ መጋራት ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ የሚያስጨብጠው ማንዋል/ብሮሸር በማዘጋጀት ነውን?	--	--	6	100%
2	ተቋሙ የወጪ መጋራትን የሚሠራ እና ሥራውን የሚያካሄድ ራሱን የቻለ የሥራ ክፍል አቋቁሟልን?	3	50%	3 /ሀዋሣ፣ ዲላ፣ ጎንደር/	50%
3	ተቋሙ ለተመረቁ እና ላቋረጡ ተማሪዎች በየበጀት ዓመቱ የተጠቀሙትን የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ሂሣብን አስልቶ ይይዛልን?	6	100%	--	--
4	ተቋሙ ደንብ ቁጥር 154/2000 ከወጣ በኋላ የክፍያ ሂሣብ ላልፈፀሙ /የአገልግሎት ግዴታቸውን ላልተወጡ ተማሪዎች ዋናውን ዲግሪ ሰጥቷልን?	4 /አዲስ አበባ፣ ባህርዳር፣ ሀዋሣ እና አዳማ/	67%	2	33%
5	ተቋሙ በደንብ ቁጥር 154/2000	6	100%	--	--

	መሠረት በመንግሥት ተመድበው የሚገቡትን ተማሪዎች ብቻ ለወጪ መጋራት ያሳትፋልን?				
6	ተቋሙ የቅድሚያ ክፍያን የሚመርጡ ተማሪዎችን ያስተናግዳልን?	2 /አዳማ፣ ሀዋሣ/	33%	4	67%
7	ተቋሙ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር በክፍያ እና በአገልግሎት ለይቶ ሪፖርት ያደርጋልን?	1	17%	5 /ጎንደር፣ ሀዋሣ፣ ዲላ፣አዳማ፣ ባህርዳር/	83%
8	ለተቋሙ በደንቡ እና በአፈፃፀም መመሪያው መሀከል ለነበረው የጊዜ ክፍተት የሚረዳ የአሰራር መመሪያ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልኮላችኋልን?	--	--	6	100%

<u>ማስገንዘቢያ</u>፣ በአጠቃላይ ኦዲት የተደረጉት ተቋማት ብዛት ስድስት ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 1.2 ከኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት፣ አሠሪ ድርጅቶች እና ከክልል/ከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች የተገኘ ትንተና

ተ.ቁ.	መግለጫ	በኦዲቱ ምላሽ የሰጡ ተቋማት ብዛት እና በመቶኛ			
		አዎ	በመቶኛ % age	አይደለም	በመቶኛ % age
1	ባለሥልጣኑ ለቅ/ጽ/ቤቶች እና ውክልና ለሰጣቸው የክልል ከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ዝርዝር ልኮ ያውቃልን?	--	--	8	100%
2	ባለሥልጣኑ የወጪ መጋራት ክፍያ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና ውክልና በሰጣቸው ከተማ/ፋይናንስ ቢሮዎች የወጪ መጋራት ክፍያ መሰብሰቡን ይከታተላልን?	--	--	8	100%
3	ባለሥልጣኑ በአዲሱ ደንብ ቁጥር 154/2000 መሠረት ውክልናውን አሻሽሎ ልኮላችኋልን?	--	--	8	100%
4	ድርጅቱ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በወጪ መጋራት ዙሪያ በሚያዘጋጀው ሴሚናሮች ላይ ተሣትፎ ያሳውቃል?	7	17%	34	77%

<u>ማስገንዘቢያ</u>፣ በአጠቃላይ ኦዲት የተደረጉት አራት የኢ/ገ/ጉ/ባ ቅ/ጽ/ቤት እና አራት የክልል/ የከተማ አስተዳደር ገቢ ሰብሳቢ ቢሮዎች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 1.3 ከአሰሪ ድርጅቶች የተገኘ ትንተና

ተ.ቁ.	መግለጫ	በኦዲቱ ምላሽ የሰጡ ተቋማት ብዛት እና በመቶኛ			
		የሚያደርጉ/ የሚይዙ	በመቶኛ % age	የማያደርጉ/ የማይዙ	በመቶኛ % age
1	ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅና በደንቡ መሠረት ከከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ሠራተኞቻቸው 10 በመቶ (1/3ኛ) ተቀናሽ	--	--	3	100%
2	በአካል ከታዩ አሰሪ ድርጅች በአዋጁና በደንቡ መሠረት ከከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ሠራተኞች 10 በመቶ (1/3ኛ) ተቀናሽ	13	59%	9	41%
3	የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ውክልና የሰጣቸውን የክልል/ከተማ ገቢዎች/ፋይናንስ ቢሮዎች ከከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የሚሰበሰቡ እና ፈሰስ	1	25%	3	75%
4	በሰርቬይ ቃለ-መጠይቅ ከተበተነላቸው አሰሪ ድርጅቶች የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር በየ3 ወሩ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሪፖርት	3	5%	19	95%
5	በአካል ኦዲት ከተደረጉት የከፍተኛ ትምርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር በየ3 ወሩ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሪፖርት የሚያደርጉ	--	--	24	100%
6	በሰርቬይ ቃለ-መጠይቅ ከተላከላቸው አሰሪ ድርጅቶች የከፍተኛ ትምርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚን ሲቀጥሩ ከተቋማት ጋር የገባውን ውል	12	55%	10	45%
7	በአካል ኦዲት ከተደረጉት አሰሪ ድርጅቶች የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚን ሲቀጥር ከተቋማት ጋር የገባውን ውል	4	36%	7	64%

ማስገንዘቢያ፣ በአጠቃላይ ኦዲት የተደረጉት ሦስት ሚኒስቴር መ/ቤቶች እና 24 የግል እና የመንግሥት መ/ቤቶች በአካል በመሄድ፣ ለ60 አሰሪ ድርጅት ቃለ-መጠይቅ

ተልኮላቸው 22ቱ ምላሽ በሰጡት ላይ እና ለአራት የክልል/ከተማ ገቢዎች/ፋይናንስ ቢሮዎች ናቸው፡፡

ከላይ በተመለከተው መረጃ ትንተና (Data Analysis) መሰረት የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን አዋጅ እና ደንብ ተፈፃሚ እንዲያደርጉ ሥልጣን እና ኃላፊነት የተሰጣቸው ባለድርሻ አካላት እንደተሰጣቸው የኃላፊነት ደረጃ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን ዓላማ በጥልቀት በመረዳት በኃላፊነት እና በተጠያቂነት መንፈስ:-

- በቅንጅት እየሰሩ አለመሆኑን፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ በሆነ መልኩ እየተሰራ አለመሆኑን፣ የመረጃ ልውውጥ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በበቂ ሁኔታ እየተሰራ አለመሆኑን እንዲሁም ከከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች መሰብሰብ የሚገባውን ያህል እየተሰበሰበ አለመሆኑን እና የተሰበሰበውም ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለታቀደለት ዓላማ እየዋለ አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡